# ለስኬታማነት ውጤታማነት

ረቢዓ አልጀረሲ እንዲህ ይላሉ፡- "አላህ (ሱ.ወ.) መልካም ሥራን ከጫማ ማሰሪያችሁ የቀረበ አድርጎታል፤ መጥፎን ነገር ደግሞ የእይታችሁ መጨረሻ ያህል አርቆታል።"

## 1) የቀን ዕረፍት (ቀይሉላ) ውሰድ

የሌሊት ሶላት መስገድ ትልቅ እድልና ውድ ንብረት ነው። ሸይጧኖች በትጋት የሚንቀሳቀሱባቸው የቀን ሰዓታት ውስጥ አንድ ሰዓትን ከፍለህ ውድ የሆነች የሌሊት ጊዜ ብትገዛ አትራፊ ነህ። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡-

((قيلوا فإن الشيطان لا تقيل))

"የእኩለ ቀን እረፍት አድርጉ (ተኙ)። ሸይጧኖች ረፍት አያደርጉምና"[1]

የቀን ሰዓታትን በጨዋታና በመጫጫህ በማሳለፍ የሸይጧንን አርዓያ ከመከተል አስጠነቅቅሃለሁ። ሐሰን አልበስሪ በገበያ ቦታ ሲያልፉ ሰዎች እኩለ ቀን ላይ እየተጯጯሁ ሲስቁና ሲጫወቱ ተመለከቱና፡- "እነኝህ ሰዎች የቀን ረፍት አይወስዱም እንዴ?" ሲሉ ጠየቁ። ረፍት እንደማይወስዱ (እንደማይተኙ) ገለፁላቸው። እርሳቸውም፡- "የሌሊት ጊዜያቸው መጥፎ የሚሆን ይመስለኛል።" በማለት በዚህ ሁኔታ ቀናቸውን የሚያሳልፉ ሰዎች የሌሊት ሶላት መስገድ እንደሚከብዳቸው ገለፁ።

## 2) ምግብ ቀንስ

አንድ ሰው ወደ ታላቁ ዓሊም ሙሐመድ ኢብን ሲሪን መጣና፡- "ዒባዳ ላይ እንዴት መበርታት እንዳለብኝ ያስተምሩኝ" አላቸው። ኢብን ሲሪንም "እስኪ የአመጋገብ ሥርዓትህን ንገረኝ?" በማለት ጠየቁት። ሰውየውም "በደንብ እስክጠግብ ድረስ እመገባለሁ" አላቸው። "ይህ የእንስሶች አመጋገብ ነው" አሉት። ሰውየው ቀጠለና "ጥሜ እስኪቆረጥ

---

[1] አቡ ነዒምና ጠበራኒ

በደንብ እጠጣለሁ" አላቸው:: "ይህ ደግሞ የከብቶች አጠጣጥ ነው:: በል ሂድና በመጀመሪያ አመጋገብህን አስተካክለህ ተመለስ:: ከዚያም ዒባዳ ላይ እንዴት መጠንከር እንዳለብህ አስተምርሃለሁ" በማለት አሰናበቱት::

የአመጋገብ ሥርዓትህን ማስተካከል ማለት ውጤቱ ይህ ነው:: ረሃብህን ማስወገድ የሚችል ያህል ከተመገብክና የምትጠጣውንም ውሃ ከመጠንክ ለዒባዳ መነቃቃት ውስጥህ ይፈጠራል:: ተቃራኒው ደግሞ ድካምና እንቅልፍን ያስከትላል::

ይህም ሲባል ረሃብን ማበረታታት አይደለም:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መንቀሳቀስ የማያስችልንና ድካም የሚያስከትልን ረሃብ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲጠብቃቸው ተማፅነዋል:: ነገር ግን ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ሱና ጋር የሚጠጣም ዓይነት የምግብ ምጠና እጅግ ተፈላጊ ነው:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ነበር ያስተማሩን:-

((بحسب ابن آدم لقيمات يقمن صلبه , فإن كان لا محالة فثلث لطعامه , وثلث لشرابه, وثلث لتفسه))

"የአደም ልጅ አካሉን ሊያቆምለት የሚችል ያህል ትንሽ ጉርሻዎች ይበቃዋል:: የግድ ከዚህ በላይ መብላት ካለበት አንድ ሶስተኛውን ለምግቡ፣ አንድ ሦስተኛውን ለሚጠጣው፣ አንድ ሦስተኛውን ለትንፋሹ ያድርግ::"[1]

ሱፍያን አሥ-ሠውሪይ የሌሊት ሶላት የናፈቃቸውን ሰዎች እንዲህ በማለት ይመክራሉ:- "ምግብን በመቀነስ አደራ እላችኋለሁ:: ያኔ የሌሊት ሶላት የእናንተ ይሆናል::" ሱፍያን ይህንን ምክር ጥሰው ራሳቸውን ሲያገኙ ነፍሳቸውን ሥርዓት የሚያስይዙበት መንገድ አላቸው:: ከእለታት በአንዷ ሌሊት ጠግበው ተመገቡና ለራሳቸው እንዲህ አሉ:- "አህያ ከቀለቡ በላይ ከተሰጠውና ከተመገበ ከዕለታዊ ስራው በተጨማሪ መስራት ይኖርበታል::" እናም ያችን ሌሊት እስከ ንጋት ድረስ በዒባዳ አሳለፏት::

### 3) የፍራሽህን ምቾት ቀንስ

---

1 አህመድ፣ ቱርሙዚና፣ ኢብን ማጀህ

ዑመር ኢብኑ አልኸጧብ (ረ.ዐ.) የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ፍራሽ ምን ይመስል እንደነበር ገልፀውልናል፡-“ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስሌን ላይ ጋደም ብለው ባለበት ወደ ቤታቸው ገባሁና እርሳቸው ዘንድ ተቀመጥኩ። ስሌኑ ላይ ሽርጣቸውን ብቻ አንጥፈዋል። ስሌኑም ጎናቸው ላይ ምልክቱን ትቷል።”

የምእመናን እናት ዓኢሻ (ረ.ዐ) ደግሞ ትራሳቸው ምን ይመስል እንደነበር ትነግረናለች፡- “ሌሊት ይተኙበት የነበረችዋ ትራስ የተሰራቸው ከቆዳ ሲሆን ውስጧ በደረቅ ገለባ የተሞላ ነበር።”ትላለች።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን የሚያደርጉት መንቃት እንዲገራላቸውና በሌሊት ሶላት ላይ መነቃቃትን ለማግኘት እንዲረዳቸው ነው። እርሳቸው ያለፈውም ሆነ የሚመጣው ወንጀል ሁሉ የተማረላቸው ነቢይ መሆናቸውን ልብ ይሏል። ዐይናቸው እንጅ ልባቸው የማይተኛ የአላህ ባሪያ ናቸው። የሌሊት ሶላት ላይ ሲቆሙ እግራቸው እስኪያብጥ የሚቆሙና ሱጁድ ሲያደርጉ የተመለከቱ ሶሓቦቻቸው ሱጁዳቸው ከመርዘሙ የነተሳ የሞቱ መስሏቸው የሚደነግጡላቸው ታላቅ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው። ኩታቸው ከትከሻቸው እስኪወድቅ ድረስ እጃቸውን ከፍ አድርገው ጌታቸውን የሚለምኑ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) ናቸው። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ለኛ ለተከታዮቻቸው መልዕክት ለማስተላለፍ ነው። በንግግራቸው የለገሱትን ምክር በተግባርም ለማፅናት በማሰብ።

ይህን ስንል ሁሉንም ሌሊቶች ፍራሽህን ትተህ መሬት ላይ ተኛ ማለታችን አይደለም። አላህ (ሱ.ወ.) ሐላል ያደረገልህን ነገር ሐራም እያደረግንብህም አይደለም። አልሙናዊ የተሰኙት ዓሊም የለገሱንን ምክር ለአንተም ለማስተላለፍ በማሰብ እንጂ፡- እንዲህ ነበር ያሉት፡- “ስንፍና የሚያሸንፈውና የእረፍት ዝንባሌው ከፍ ላለ ሰው የመኝታ ፍራሹን በጣም የሚመች ባያደርግ መልካም ነው። ምክንያቱም ይህን ማድረጉ ለእንቅልፉ መብዛት፣ ለከፍተኛ መዘናጋትና አስፈላጊ ከሆኑ መልካም ስራዎች ለመሳነፍ ዋነኛ ምክንያት ይሆናልና።”

አንተ የሌሊት ሶላትን ትተህ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ የምትዋኝ ወንድሜ ሆይ! ሌሊቱ በእንቅልፍህ ብዛት ተማረረ፣ ፍራሹም እንቅልፍህ

ስልችቶት አቤቱታ አሰማ፣ ሑረልዐይን ስለርሷ ባለህ ግድ የለሽነት ተገረመች፣ ጠባቂ መላኢኮችህ የሚያመልጥህን ትርፍ በማየት አለቀሱ:: ወዳጆችህን ውደድ፤ የናፈቁህን ሑረልዐይኖች ለማግኘት ልፋላቸው:: ጌታህ ፊት ቁምና ለእዝነትና ምህረት ነፋሱ ራስህን አቅርብ:: በዚህ ሁኔታ ባለፍክባት ቅፅበት የስኬትን ማማ ትቆናጠጥ ይሆናል:: የፊርዐውን ድግምተኞች ኢማናዊ ምጥቀት ቅፅበታዊ መሆኑን አትዘንጋ::

## 4) መልካም ጓደኛ ያስፈልግሃል

ሐሰን ኢብን ዐሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ በዘገቡት ሐዲሥ አባታቸው ዐሊይ ኢብን አቢጧሊብ የነገሯቸውን ሲያስተላልፉ (ዐሊይ ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ "ከዕለታት በአንዱ ሌሊት ከባለቤቴ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ ፋጡማ (ረ.ዐ) ጋር ተኝቼ ባለሁበት ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) በር አንኳኩ:: እናም "አትሰግዱም እንዴ?" አሉን" እኔም "አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ነፍሳችን በአላህ እጅ ናት:: እርሱ ከፈለገ ይቀሰቅሰናል" አልኳቸው ይህንን ስላቸው አንድም ነገር ሳይመልሱልኝ ጥለውን ሄዱ:: ፊታቸውን አዙረው በሚሄዱበት ጊዜ ጭናቸውን በእጃቸው እየመቱ እንዲህ ሲሉ ሰማኋቸው:-

"وكان الإنسان أكثر شيء جدلا"

"የሰው ልጅ ክርክረ ብዙ ሆነ::"[1]

ጦበራኒ ይህንን ሐዲሥ አስመልክተው የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል:- "የሌሊት ሶላት ክብደት ባይኖረው ኖሮ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጃቸውንና የአጎታቸውን ልጅ አላህ ለፍጡራን የእረፍት ሰዓት ባደረጋቸው የሌሊት ጊዜያት ባልቀሰቀሷቸውም ነበር:: ዳሩ ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከእረፍት ይልቅ የእነኛን ሰዓታት የአምልኮት ትሩፋት ማግኘታቸውን መረጡላቸው:: ይህ ደግሞ የአላህ ትዕዛዝ ከመተግበርም አኳያ ነበር:-"

﴿وَأۡمُرۡ أَهۡلَكَ بِٱلصَّلَوٰةِ﴾ طه: ١٣٢

"ቤተሰብህንም በስግደት እዘዝ::"(ጧሃ: 132)

---

[1] ቡኻሪና ሙስሊም

ከዚህ ሁሉ በመነሳት እንዲህ እልሃለሁ፡- በኸይር ነገር ላይ የሚያግዝህ ጓደኛ ይኑርህ፡፡ . . . በጥልቅ የመዘናጋት ጉድጓድ ውስጥ በወደቅህ ጊዜ ድምፅህን ከፍ አድርገህ የእርዳታ ጥሪ አሰማ፤ ድረሱልኝ! ድረሱልኝ! በል.. ምናልባትም ነቢዩላህ ዩሱፍን ከጉድጓድ እንዳወጡት ዓይነት ነጋዴዎች ደርሰው የውሃ ማውጫ ገመዳቸውን ይልኩልህ ይሆናል... ገመዱን ስታገኝ በእሱ ላይ መንጠልጠልን አደራ እልሃለሁ፡፡ አልያ ግን የእርዳታ ጥሪ አሰምተው የሂዳያን ጎዳና ከመፈለግ በመቆጠባቸው በጥመት ጉድጓድ ውስጥ ተውጠው እንደቀሩት እልፍ አዕላፋት እንዳትሆን ያለኝን ስጋት እገልፅልሃለሁ፡፡ እንዲያ ከመሆንም አስጠነቅቅሃለሁ፡፡ የንጋት በፊት ምህረት ለማኞችን ከሩቅም ቢሆን ድምጽህን ከፍ አድርገህ ጥራቸው፤ ምናልባትም ያዝኑልህ ይሆናል፤ የሙተሀጂዶችን (የሌሊት ሰጋጆችን) ጋላቢ ፈረስ ቀረብ በል፤ ምናልባትም ጓደኛቸው ያደርጉህ ይሆናል፡፡ የሌሊት ቋሚዎችን እንዲህ ስትል ተጣራ፡- “አብራችሁ ውሰዱኝ... ጓደኛችሁ አድርጉኝ... ከናንተ አንዱ አድርጉኝ... ብቻዬን አትተዉኝ... እባካችሁ አስታርቁኝ... የወንጀሌ ሸክም ተጭኖኛል አግዙኝ... ስሜቴ በየአቅጣጫው ከቦኛልና አትጣሉኝ... ነፍስያዬ እያጠፋችኝ ነውና አሳልፋችሁ አትስጡኝ... እናንተ ቀልባችሁን አግኝታችኋልና ያላገኘን እዘኑለት... ጊዜያችሁንና እረፍታችሁን መሰዋት ችላችኋልና መሰዋት ያልቻልኩት ወንድማችሁን አስተምሩኝ... ወንድሞቼ ሆይ! እናንተ አላህን የመገዛት ከበርቴዎች ናችሁ ለድሆች መጽውቱ፡- “إن الله يجزي المتصدقين!” “አላህ ምጽዋት የሚሰጡትን ይመነዳል፡፡”... እናንተ የአር-ረሕማን ወዳጆች ሆይ! ለወዳጃችሁ ባሪያ እዘኑለት፤... እውነተኛ ወዳጅ ወዳጁን ለማስደሰት የማይሆነው የለም፤ የወዳጁን ባሮች ለመርዳትም የቻለውን ሁሉ ያደርጋል፤... አላህ ምንዳችሁን ይክፈላችሁና ጥሪዬን የሚቀበል ማን ይሆን?!”

እንዲህ ሊያግዝህ የሚችል ዓይነት ጓደኛ በቅርብ አለመኖሩ አያሳስብህ፡፡ የዘመኑን መልካም ቴክኖሎጂ ተጠቀም፡፡ ያን ወንድምህን የትም ሆኖ በሌሊት ሰዓታት ደውሎ ይቀሰቅስህ ዘንድ አደራ በለው፡፡ ምናልባትም የዚህ ወንድምህ የስልክ ጥሪ ከገባህበት ጥልቅ እንቅልፍ አንቅቶ ከታላላቆቹ የአላህ ባሮች ተርታ ያሰልፍህ ይሆናል፡፡

## 5) ቀንህ ይመር... ሌሊትህ ያምራል

አንድ ሰው ኢብራሂም ኢብን አድሃም ዘንድ መጣና፡- "እኔ ሌሊት ተነስቼ ዒባዳ ማድረግ አልቻልኩም፡፡ እባክዎ መድሃኒቱን ይንገሩኝ፡፡" አላቸው፡፡ እርሳቸውም የሚከተለውን መድሃኒት ነገሩት፡- "በቀን ሰዓታት አላህን አትወንጀለው (ታዘዘው)፤ ያኔ በሌሊት ሰዓታት እርሱ ዘንድ ያቆምሃል፡፡ የሌሊት ሰዓታት እርሱ ዘንድ ታላቅ ክብር አላቸው፤ ይህ ክብር ደግሞ ለወንጀለኞች የተገባ አይደለም፡፡"

ታላቁ ዓሊም ፉደይል ኢብኑ ዒያድም ተመሣሣይ አባባል አላቸው፡- "በሌሊት ተነስተህ መስገድና በቀን መፆም ከተሳነህ አንተ ከመልካም ስራ የተነፈግክና ተጠፍንገህ የታሰርክ መሆንህን እወቅ፡፡ ጠፍንጎ ያሰረህ ደግሞ ወንጀልህ ነው፡፡"

የሌሊት ሶላት ጠቢብ እና የቀን ፆም ተምሳሌት የሆኑት ሐሰን አልበስሪ ሶስተኛ ተመሣሣይ ምክራቸውን ይለግሳሉ፡-

"አንድ ሰው የሌሊት ሶላት መስገድን አይተውም በሰራት አንዲት ወንጀል ሳቢያ ቢሆን እንጅ፡፡ ስለሆነም ፀሐይ በጠለቀች ቁጥር ራሳችሁን ገምግሙና ወደ አላህ ተመለሱ፡፡ በሌሊት ሰዓታት መቆም ትችሉ ዘንድ፡፡"

ማንኛውም ከመልካም ነገር የተነፈገ ሠው ቅጣት ላይ ነው፡፡ የቅጣት ደግሞ ደረጃዎች አሉት፡፡ ከባዱ ቅጣት ግን የሚቀጣው ግለሰብ እየተቀጣ መሆኑ ሳይሰማው ሲቀር ነው፡፡

እናንተ የሌሊት ቋሚዎች ሆይ! ለእንቅልፋሞቹ አማልዱ፡፡ እናንተ ባለህያው ልቦናዎች ሆይ! ለሙታን የአላህን እዝነት ለምኑላቸው፡፡ የሌሊት ሶላትን ያጣ ምን አገኘ?! እሱን ያገኘስ ምን አጣ?!

የሙተሃጂዶችን ብርሃን የሚመስል ብርሃን ፈፅሞ የለም፤ አዛኙን ጌታቸውን ለብቻቸው አገኙትና ከብርሃኑ አለበሳቸው፡፡

የእንቅልፋሞች ጨለማ ዓይነት ጨለማ ፊፀሞ የለም:: . . . በሌሊት መስነቁን ተውና የቀን መብራታቸው ጠፋ፤ እናም ፊታቸው ብርሃን አልባ ሆነ::

ምንኛ ያምራል ውበታቸው፥
ሌሊት ሲሰግዱ ላያቸው::
ከኮከብ ላቀ ብርሃናቸው::
የመጠቀ ነው ሰብዕናቸው::
ሲነሱ ከንጋት በፊት፣
ፈጣሪያቸውን ለማስደሰት::
የፊታቸው ብሩህ ጮራ
እንደ ፀሐይ አበራ::

## 6) የእቃውን ምርጥነት ስትረዳ ዋጋውን መክፈል ይቀልሃል

የዚድ ኢብኑ ሃሩን እንዲህ ይሉ ነበር፡-

"ስለ ሌሊት ሶላት ሳስብ የሚታወሰኝ ሌሊቱን ሙሉ በጥበቃ የሚያሳልፉ ዘበኞች ናቸው:: እነኝህ ሰዎች ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ አጥተው የሚከፈላቸው ክፍያ ሲሶ ዲርሃም ያህል ነው:: ታዲያ አንተ አንዲት ሌሊት ብቻ እንቅልፍ በማጣትህ ጀነትን ማግኘት ትፈልጋለህ እንዴ? ምናልባትም እኮ ይህችው ዒባዳህ ሲሶ ዲናር የማትመጥንና በጌታህ ላይ የተመፃደቅባት ትሆናለች::"

ትርፍ ምግብ በመመገቡ ምክንያት የሌሊት ሶላትን የሸጠ፣ ለእንቅልፉ ሲል የንጋት በፊት ነፋሻ አየርን የሰዋ፣ ለትንሽ ደቂቃዎች እረፍት ሲል ከታጋዮች ጎራ የሸሸ ሰው በእጅጉ ያስገርማል::

ስማኝ ወንድሜ!፡-

የተሀጁድ[1] ጥቂት ደቂቃዎችን በነቢዩ ሱለይማን (ዐ.ሰ.) ንግስናና በኑሕ (ዐ.ሰ.) ዕድሜ ብትለውጥ አንተ በእርግጥ ከከሳሪዎች ነህ። ነፍስህን እንዲህ ስትል ገስፃት፡-

"ነፍሴ ሆይ! እንደ ህልም በፍጥነት ለሚያልፉ ቀናት አትንበርከኪ። በመልካም ስራ ላይ ታገሺ። በቆራጥነት ወደ ፊርደውስ ገስግሺ፣ እንቅልፍን ወዲያ በይ፣ እውነተኛ ህይወት ያለው ፊት ለፊትሽ ነውና!"

የሕያ ኢብኑ ሙዓዝ እንዲህ ይላሉ፡-

"በዚህች ምድራዊ ዓለም የአንድ ሰው ዕድሜ ምንም ያህል ቢረዝም ከጀነት ኑሮ አንፃር ሲወዳደር የአንድ ትንፋሽ ያህል ነው፣ እናም ለዘለዓለማዊ ኑሮ የሚያበቃውን አንድ ትንፋሽ ያባከነ በአላህ እምላለሁ- በእርግጥ እርሱ ከከሳሪዎች ነው።"

ሰለፎች ይህንን እውነታ ተረዱ፣ እርግጠኛም ሆኑ። ሁሉም ነገር ተገለፀላቸውና ስራ ቀለላቸው፣ የጀነት ጉጉት ማነቃቂያቸው ሆነ፣ እንቅልፍ ማጣት አረካቸው፣ ልፋታቸው ደስታ ሰጣቸው፣ አላህ ግባቸው ሆነ፣ እነርሱ ጓዛቸውን ጀነት ላይ እስኪያራግፉ ፈፅሞ እረፍት አልነበራቸውም።

እናም ያጣህው ምን ያህል ውድ ነገር እንደሆነ እወቅ፣ ባመለጠህ ታላቅ ነገር ልታለቅስ ይገባሃል፣ ያለፈህን ለማካካስ መፍጠን ይኖርሃል፣ ምናልባትም ቅፍለቱ ላይ ትደርስ ይሆናል። ባይሆን በወንጀል የወፈረ ሰብዕናህን ከወንጀል በመራቅ ማክሳት ይጠበቅብሃል፣ በዚህ ውፍረት የምትፈልገውን ያህል በፍጥነት መሮጥ አይቻልህምና። ይህም ከክፍያዎቹ የመጀመሪያው ይሆናል።

## 7) የሰለፎችን ታሪክ አጥና

[1] ተሀጁድ፡- ማለት የሌሊት ሰላት ማለት ነው።

የሰለፎች[1] ፀሐይ ስትወጣ የኸለፎች[2] ክዋክብት ይጨልማሉ። ዜናቸው ሕይወት ነው፤ በህይወት በነበሩባቸው ጊዜያት በምላሳቸውና በተግባራቸው ወደ አላህ ጥሪ አደረጉ፤ ወደ አኼራ ሲሄዱ ደግሞ ምላሳቸው ዝም አለና የተግባራቸው ንግግር ቀጠለ፤ እናም በህይወታቸውም ሆነ በህልፈታቸው ወደ አላህ (ሱ.ወ.) መንገድ ተጣሪዎች ሆኑ። ዛፋቸው ጥላው የተስፋፋ፣ ፍሬው የተንዥረገገና ጠቀሜታው የላቀ ከመሆን አልነጠፈም፤ እስከ አሁንም ፍሬ ከመስጠት አልተቆጠበም። ብቸኛን ያረጋጋል፤ የጠመመን ይመራል፤ የተርበደበደን ያፀናል፤ የተጠማ ሁሉ ወደ ምንጩ ጎራ ይላል።

✓ አስ-ሲሪ አስ-ሰቀጢ የተባሉት ሰለፍ ሌሊቱ ሲመጣ ከመጀመሪያው ጀምሮ በአምልኮ ተግባራት ይተጋሉ፤ ሰዓቱ በጨመረ ቁጥር ትጋታቸውን ይጨምራሉ፤ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ድካምና እንቅልፍ ሲያሸንፋቸው ስቅስቅ ብለው ማልቀስ ይጀምራሉ።

✓ የሷሊህ ኢብን የሕያ ልጆች የሆኑት ዐሊይና ሐሰን እንዲሁም እናታቸው የሌሊቱን ሰዓታት ከሦስት ይከፍሉት ነበር። ዐሊይ የመጀመሪያውን አንድ ሦስተኛ ሌሊት በሶላት ያሳልፍና ይተኛል፤ ሐሰን ደግሞ ቀጣዩን ክፍል ያሳልፍና ይተኛል፤ እናታቸው የመጨረሻው የሌሊቱ ክፍል ላይ ትነሳና ትሰግዳለች። ከዚያም እናታቸው ወደ አኼራ ስትሄድ ሌሊቱን ሁለቱ ወንድሞች ተከፋፈሉትና እስከ ንጋት ድረስ በዒባዳ ያሳልፉ ነበር። በመጨረሻም ዐሊይ ወደ አኼራ ሄደ። ሐሰን ሙሉውን ሌሊት በዒባዳ ማሳለፍ ጀመረ።

✓ የመንሱር ኢብን አልሙዕተር ጎረቤት ሴት ልጅ በአንድ ወቅት አባቷን 'አባቴ ሆይ- በመንሱር ኮሪደር ላይ ተተክላ የነበረችዋ እንጨት የት ሄደች?' በማለት ጠየቀች። ሰውዬውም ልጃቸውን ሲያስረዱ:- "ልጄ ሆይ! ያ ያየሽው እኮ እንጨት አልነበረም፤ እርሱ መንሱር ነው፤ የሌሊት ሶላት ሲሰግድ ነበር።" (መንሱር ለረጅም ጊዜ ከመቆማቸው የተነሳ ለሚመለከታቸው ሰው የተተከለ እንጨት ይመስሉ ነበር።)

---

ሰለፍ- ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን ጀምሮ እስከ 300 ዓመታት የነበሩ ትውልዶች
ኸለፍ- ከ300 ዓመት በኋላ የመጡት ትውልዶች በሙሉ

✓ በማንኛቸው እንደምንደመም አናውቅም:: በሪያሕ አልቀይሲ ወይስ በባለቤቱ? ታሪኩ እንዲህ ነው:- ሪያሕ ኢብኑልቀይሲ አንዲትን ሴት አገባ፤ የመጀመሪያ ሌሊት ላይ ሊፈትናት ፈለገና ተኛ:: የመጀመሪያው አንድ አራተኛ ክፍል ሲሆን ለሌሊት ሶላት ነቃች:: እርሱንም ጠራቸው:- "ሪያሕ ሆይ! ተነስ" አለችው:: "እሽ እነሳለሁ" ብሏት ተኛ:: ጥላው መነሳት አልቻለችም:: ሁለተኛው አንድ አራተኛ ሲሆን አሁንም ነቃችና "ሪያሕ ሆይ! ተነስ" አለችው:: "እሽ እነሳለሁ" አላት፤ ግን አልተነሳም:: ጥላው መነሳት አልፈለገችም:: ሶስተኛው የሌሊቱ ክፍል ሲሆን ነቃችና "ሪያሕ ሆይ! ተነስ" አለችው:: "እሽ እነሳለሁ::" አላት እርሷም:- "ሌሊቱ አለፈ፤ አንተ በተኛህበት ደጋግ የአላህ ባሮች ዘብ ቆመዋል:: ማን ይሆን አንተን እንዳገባ ያሳሳተኝ?" ስትል ተበሳጭታ ተናገረችና ቀሪውን አንድ አራተኛ ሌሊት በሶላት አሳለፈች::

የንጋት በፊት ጊዜ ነፋሻ አየር ውብ ጠረኑን ያገኘው ከእነኝህ ታላላቅ የአላህ ባሮች ትንፋሽ ነው:: ፀሐይ ሰዓቷን ጠብቃ መጥለቋ የእነርሱን ብርሃን አፍራ ነው፤ ከዋክብት ሰማዩን ሞልተው መታየታቸው እነርሱን ለማግኘት ጓጉተው ነው፤ የሌሊቱ አንድ ሶስተኛ ክፍል የተላቀው ጌታችን ወደ ቅርቢቱ ዓለም ሰማይ መውረዱ ለእነርሱ ሲል ነው፤ ምንኛ ክብራቸው ላቀ?! ምንኛ ደረጃቸው ከፍ አለ?!

## 8) የምር የሆነ የመነሳት ሀሳብ ይኑርህ

ሀሳብህ የእውነት ከሆነ፣ የምርህን ለመነሳት ከቆረጥክና ጌታህ ፊት ለመቆም ከልብህ ከጓጋህ፣ አንድ የሆነ ነገር እንደሚቀሰቅስህ እርግጠኛ ሁን:: ምናልባት የንፋስ ሽውታ፣ የድመት ሩጫ፣ የህፃን ልጅ ለቅሶ ሊሆን ይችላል:: ይህ ሁሉ ባይሆን እንኳ ምክንያቱ ያልታወቀ የእንቅልፍ እጦት ሊቀሰቅስህ ይችላል::

ከዚህ ሁሉ የምር ሀሳብ፣ ቆራጥነትና አስፈላጊ ምክንያቶችን ካሟላህ በኋላ ሳትነሳ ከቀረህ አትዘን፤ አላህ (ሱ.ወ) በአንተ ላይ ሶደቃ (ምፅዋት) ችሮሃልና::

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያሉትን አስታውስ፡-

((من أتى فراشه وهو ينوي أن يقوم يصلي من الليل فغلبته عينه حتى يصبح كتب له ما نوى , وكان نومه صدقة عليه من ربه))

"ሌሊት የመስገድ ሀሳብ ሰንቆ ለመተኛት ወደ ፍራሹ የሄደ ሰው ከዚያም እስከ ንጋት ድረስ እንቅልፍ ቢጥለው የሀሳቡን ያህል ምንዳ ይፃፍለታል፤ እንቅልፉም ከጌታው ለእርሱ የተሠጠ ሶደቃ ይሆንለታል።"[1]

ተኝቶ አድሮ ምንዳው ከሰጋጆች የሚልቅ ሰው ምንኛ ይገርማል?! ፆም የፈታ ሆኖ ከፆመኛ ሰው የበለጠ አጅር ባለቤት የሆነ ሰው ምንኛ ያስደምማል?! ፍራሹ ላይ ሞቶ የፍልሚያ ሜዳ ላይ ከተገደለው ሰው የበለጠ ደረጃ ላይ የደረሰ ግለሰብ ምንኛ ድንቅ ሰው ነው?! . . .

አቡ አድደርዳእ (ረ.ዐ) መገረማቸውን እንዲህ ይገልፃሉ፡-

"የብልሆች እንቅልፍና ፆም ፍች ምንኛ ያምራል?! የቂሎችን እንቅልፍ እጦትና ፆም አስከንድቶ ይበልጣል። አላህን የሚፈራ ሰው ብናኝ ያህል መልካም ስራ፤ የተራራ ያህል የገዘፈ ራሱን ሸንጋይ ከሆነ ሰው ዒባዳ እጅግ በጣም በላጭና ተመራጭ ነች።"

ከላይ የሰማሽው ነገር አፍህን በግራሞት አስከፍቶ ከሆነ ለተጨማሪ ማብራሪያ ኢብኑልቀይምን ጋብዘናል። ለዚህ ጉዳይ ተገቢ ጠቢብ ናቸውና። እንዲህ ይላሉ፡-

"ብልህ ሰው በምር ኒያ፣ እውነተኛ ቆራጥነት፣ ከፍተኛ የተነሳሽነት ስሜትና ፍላጎትን ፍፁም ለአላህ በማድረግ ረጅምን ጉዞ ያሳጥራል። ትንሹ ስራው ልቡ ኦና የሆነ ሰው በከፍተኛ ድካምና ረጅም ጉዞ ከሚከውነው እጥፍ ድርብ ይበልጣል። ምክንያቱም የአላህ ፍቅርና ፍፁም ቆራጥነት ድካምን የማስወገድና ጉዞውን አስደሳችና ፈጣን የማድረግ አቅም አላቸውና። ወደ አላህ በሚደረገው ጉዞ መቅደም የሚቻለው ከልብ በሆነ እውነተኛ ፍላጎትና ከፍተኛ የመነሳሳት ስሜት

[1] አንነሳኢ፣ ኢብኑ ማጃህ፣ ኢብን ሒባንና ሃኪም እንደዘገቡት

ነው:: እነኝህን መስፈርቶች የራሱ ማድረግ የቻለ ግለሰብ በጣም ብዙ ስራ ከሚሰራው ሰው የበለጠ በውድድር በከፍተኛ ርቀት ሊቀድም ይችላል::”

## *9) ሥርዓቱን ጠብቅ*

የአተኛኝ ሥነ-ሥርዓቶችን ጠብቅ:: ለዝርዝሩ ሁለተኛውን ስምምነት ተመልከት::

## የስምምነቱ መጨረሻ

### የመደበበቅና ግልፅ የማውጣት መርህ

መልካም ሥራህን ካጠናቀቅክ በኋላ የሚስጥር ካዝና ውስጥ አስቀምጠው፤ በኢኽላስ ቁልፍ ዝጋበት፤ በሥራህ ላይ ሸይጧንን አትተማመነው፤ ምናልባትም ሥራህን ሊዘርፈው ይችላል:: ከሚስጥርነት ወደ ግልፅነት፤ ከግልፅነት ወደ ሪያእ (ይዩልኝ) ማህደር ሊያሸጋግረው ይጥራል:: ያ ከሆነ ደግሞ 'የመልካም ሥራ መዝገቤ ላይ ተጻፈልኝ' ብለህ ያሰብከው ሥራ ወደ ወንጀልነት ሊቀየር ይችላል:: ምናልባት ሥራህን ይፋ ማውጣትህ አርአያ በሌለበት ሁኔታ ሰዎች እንደበጎ አርአያ ሊወስዱት ይችላሉ ከሚል ጥሩ አስተሳሰብ ሊሆን ከቻለ የሚከተለውን መርህ ማንበብ ይኖርብሃል:: አቡ ሓሚድ አልገዛሊ ከጥልቅ ተሞክሯቸው የሚያበረክቱልህን ውድ ስጦታ ሳትረዳ ሥራህን ይፋ ከማውጣት አስጠነቅቅሃለሁ:: ማንኛውም ወደ አላህ የሚደረግ የውድድር ተሣታፊን እንዲህ ሲሉ ያሳስባሉ –አል-ገዛሊ::

“ልቡን ሊፈትሽ ይገባዋል፤ ምናልባትም ድብቅ ሪያእ ሊኖርበት ይችላል:: ለአርአያነት ዓላማ ባይሆንም ይፋ እንዲያደርግ ሊገፋፋውም ይችላል፤ ምናልባትም መልካሙን ሥራ ፈጥኖ እንዲፈፅም ያደረገውና አርአያ እንዲሆን የገፋፋው ይኼው የሪያእ ስሜቱ ሊሆን ይችላል:: ፍፁም ሥራቸውን ለአላህ የሚያጠሩና ጠንካራ ሰዎች ሲቀሩ ይህ ማንኛውም ስራውን ይፋ የሚያደርግ ሰው ግለሰብ ባህሪ ነው:: እነርሱ ደግሞ በቁጥር እጅግ አናሳዎች ናቸው:: እናም ሳይታወቀው የመጥፋት አደጋ ሊከሰትበት ይችላልና ደካማ የሆነ ሰው ራሱን ሊያታልል አይገባም:: የእንዲህ ዓይነት ደካማ ሰው ምሳሌው ልምድ በደንብ ያላካበተ ዋናተኛ ዓይነት ነው:: ይህ ዋናተኛ በርካታ ሰዎች እየሰጠሙ በመመልከቱ አዘነላቸው:: ወደነርሱ እየዋኘ ሲጠጋቸው ሁሉም እርሱ ላይ ተንጠላጠሉ፤ እርሱም እነርሱም ሰጠሙ:: ውሃ ውስጥ መስጠም የሚያስከትለው ዓለማዊ ስቃይ ነው፤ በሪያእ /ይዩልኝና ይስሙልኝ/

የሚመጣው ጥፋት የዚሁ ያህል ቢሆን ጥሩ ነበር፡፡ ግና ቅጣቱና ስቃዩ ዘለዓለማዊ ነው፡፡ ይህ ነጥብ የታላላቅ ዑለማዎችና የአላህ ተገዥዎች ማዳለጫ ቦታ ነው፡፡”

6

# ስምምነት ስድስት

## ትዕግስት
## የስኬት ቁልፍ



ጽጌረዳ ስቃይን ተቋቋመች። በዙሪያዋ ያሉ እሾሆች የሚያደርሱባትን ችግር ታገሰች። መከራን አልፋ ለፍካት በቃች። በዚህም የታላላቅ ቤቶች ሳሎን ውስጥ በክብር ተቀመጠች። የውበት ተምሳሌት ለመሆን ቻለች። እናም ከጽጌረዳ የበለጠ ፍቅርን ገላጭ ስጦታ ማግኘት ይከብድሃል። በአንፃሩ ሳር ያለውጣ ውረድ በሰላም መኖርን መረጠ። ችግርን መጋፈጥ አልፈለገም። በውጤቱም የአህዮች መላፊያ ሆነ። የከብቶች ግጦሽ መሆን ዕጣ ፈንታው ሆነ። እጅጉን ረከሰ። እግሮች እንዳሻቸው ረገጡት። በመጨረሻም የውርደት ተምሳሌት ሆነ።

# ስምምነቱ ከመተግበሩ በፊት

## ፊት ለፊት

ኢብኑል ቀዪም እንዲህ ሲሉ ፊት ለፊት ይጋፈጡሃል፡-

“ምስጋናህ የተሰጠህን ቀለብ አይመጥንም፡፡ የተቀለበችውን ያክል የማታገለግል የጋማ ከብት አትባረክ፡፡ ህሊናህ ቀሪን ችላ ብሎ ጠፊን ከመረጠ አስተውሎትን እንደተነፈገ እወቅ፡፡ ልብህ ከአላህ ፍቅርና እርሱን ከመገናኘት ዝግጅት ተራቁቶ በምትኩ የዱንያ ፍቅርና በእርሷ ላይ መርካት ከሰፈነበት ከእውነታ የተጋረደ መሆኑን ተገንዘብ፡፡ ዓይንህ በድርቅ ከተመታ የድርቁ መንስዔ የልብህ መድረቅ መሆኑን አስተውል፡፡ ከአላህ በእጅጉ የራቁ ልቦች፥ ደረቅ ልቦች ናቸው፡፡ ሌሎቹ እየተወደዱ አንተ ካልተፈለግክ፥ ሌሎቹ እየተቀረቡ አንተ ካልቀረብክ በርግጥም የተገለልክ እና የተቀጣህ መሆኑን እወቅ፡፡”

## የስምምነቱ ትርፎች

መከራ ሲመጣብህ አንተ ዘንድ ሊያርፍ እንደመጣ እንግዳ ቁጠረው፡፡ ታዲያ ይህንን እንግዳ ተቀብለህ በሚገባ ካስተናገድከው፣ "ሶብር" የሚባል መጠጥ ካቀረብክለት፣ ምላስህ ፍፁም ክፉ ሳይወጣውና ልብህ በፍፁም ሳያማርር አስተናግደህ ከሸኘኸው፣ መላኢኮች እንዴት ያወድሱህ?! በመዝገባቸው ላይ ቸርነትህን መዝግበው ስታገኝ ምንኛ ትደሰት?!

ሶብር በመከራ ጊዜ መራር ቢሆንም መጨረሻው ግን ከማር የጣፈጠ ነው፡፡

ከጣፋጭ መጨረሻዎቹ የሚከተሉት ትርፎች ይገኛሉ፡-

### 1. የአላህ ፍቅር

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلصَّٰبِرِينَ﴾ آل عمران: ١٤٦

*"…አላህም ትዕግስተኞችን ይወዳል፡፡" (አሉ ዒምራን፡ 146)*

ወዳጁን የሚቀጣ፣ ፍቅሩን የሚቆርጥና ከወዳጁ መራቅን የሚመርጥ ወዳጅ አይተህ ታውቃለህን? አላህ (ሱ.ወ) ለሙእሚን ባሮቹ አዛኝና ርኅሩኅ ነው፡፡ የሚፈትናቸው ወንጀላቸውን ሊያፀዳላቸውና ከጀሀነም ቅጣት ሊያድናቸው ነው፡፡ የሙከራ ጊዜያቸው ቅጽበታዊ ሲሆን –ዱንያ ራሷ ቅጽበታዊ ነችና– ሙከራውን ካለፉ ግን ዘለዓለማዊ ተድላ ያጎናጽፋቸዋል፡፡

ስለዚህም ሶብር (ትዕግስት) የአላህን ውዴታ ያገኙ ቅርብ ባሪያዎች ብቻ ሊታደሉት የሚችሉት ታላቅ ስጦታ ለመሆን በቃ፡፡ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

*"አንድ ሰው ከሶብር የበለጠ መልካም ስጦታን አልተሰጠም፡፡" (ቡኻሪና ሙስሊም)*

አር-ራፊዒይ ከነቢያዊው ትምህርት ቤት የተመረቁ ታላቅ ዓሊም ናቸው። የንግግራቸው መልዕክት በሳል የመሆኑ ሚስጥርም ይኸው ነበር። እናም የኢማን ልብስ ለብሰው መከራ ሲገጥማቸው ልብሳቸውን አውልቀው የሚጥሉና በማማረር ሽማ የሚሽፋፈኑ ግለሰቦች በእጅጉ አስገረሟቸው። አግራሞታቸውንም እንዲህ ሲሉ ገለፁ:- "በአንድ ሙእሚን ሕይወት ውስጥ ሶብር የማያስፈልገው ምን ነገር አለ? ሙእሚን ፈተና ገንዘቡ መሆኑን ይረዳል። በእርግጥ የገንዘብ የሚቀመጠው ኪሱ ሲሆን፥ ፈተና ግን አካሉ ላይ ነው።"

## 2. ገደብ የለሽ ምንዳ

ጌታችን አላህ ጥራት ይገባው! በቸሮች ልብ የቸርነትን ዛፍ ተክሏል። በለጋሾች መዳፍ የልገሳን ፍሬ ዘርቷል። የቸርነት ሁሉ ምንጭ የልግስና ሁሉ መነሻ እርሱው ነው።

ከቸርነት ፏፏቴው አንዱ ደጋግ ባሮቹ (ሷሊሖች) ትዕዛዙን ሲጠብቁና በዚህም ላይ ሲታገሱ በሽልማት ማንበሽበሹ ነው።

﴿وَلَنَجْزِيَنَّ ٱلَّذِينَ صَبَرُوٓاْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ﴾ النحل: ٩٦

*"እነዚያንም የታገሱትን፥ ይሠሩት በነበሩት በመልካሙ፥ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።" (አን-ነሕል: 96)*

ምንዳውን አንቧቧላቸው። ስጦታውን አነባበረላቸው። መልካም ሥራ የሠራ ባሪያውን –ምንም እንኳ ሥራዎቹ ደረጃቸው ቢለያይም፣ የኢማኑ ጠለል ከጊዜ ጊዜ የሚለዋወጥ ቢሆንም፥ ቸሩ አላህ (ሱ.ወ) በበላጩ ሥራ መለኪያ ምንዳውን ከፈለው።

ሌላው የአላህ (ሱ.ወ) ቸርነት መገለጫ የሠራተኞችን ምንዳ በገደብ ተመጥኖ መክፈሉ ሲሆን የታጋሾች ደመወዝ ግን የሚከፈለው ያለምንም ገደብ መሆኑ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል:-

﴿إِنَّمَا يُوَفَّى ٱلصَّٰبِرُونَ أَجْرَهُم بِغَيْرِ حِسَابٍ﴾ الزمر: ١٠

*"ታጋሾቹ ምንዳቸውን የሚሰሰጡት ያለገደብ ነው፤»" (አዝ-ዙመር: 10)*

"ያለ ግምት" የሚለው በአላህ መለኪያ ምን ያህል ይሆን? የሰው ልጅ አዕምሮ ይህንን ምንዳ ለማሰብ አቅም የለውም።

በጣም የሚገርመው ነጥብ አላህ እጅግ በጣም ቸር ነውና ፈተናው በበረታ ቁጥር ስጦታው ይበልጥ የተነባበረ ይሆናል። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ነበር ያሉት፡- "ምንዳው ታላቅ የሚሆነው ፈተናው ከመክበዱ (ከመብዛቱ) ጋር ነው።" (ቱርሙዚና ኢብን ማጃህ)

## 3. *መረጋጋትን የሚያስገኝ አብሮነት*

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلصَّٰبِرِينَ ﴾ البقرة: ١٥٣

*"አላህ (በእርዳታው) ከታጋሾች ጋር ነውና።" (አል-በቀራህ፡ 153)*

በዚህ አንቀጽ የተጠቀሰው አብሮነት የዕውቀትና የማካበብ አብሮነት ብቻ አይደለም። የእገዛ፣ የእርዳታ፣ የመከላከልና የማሸነፍ (የማገዝ) አብሮነትንም ጭምር ያጠቃልላል። ይህ አብሮነት ለባሪያው የውስጥ መረጋጋትንና የልቦና ስፋትን ይቸራል።

ኃያልና አሸናፊ የሆነው ጌታ እርዳታና አብሮነት ከፍተኛ በራስ መተማመንን ያጎናፅፋል። የአላህ አብሮነት ለታጋሾች ሲረጋገጥ በዚሁ አንቀጽ መሠረት ድልን መቀዳጀት ተፈጥሯዊ ውጤት ነው። ሶብር (ትዕግስት) እና ነስር (ድል) የአንድ ዛፍ ቅርንጫፎች፣ የአንድ ጋት ጡቶች፣ አብሮ አደግ ጓደኞችና የማይለያዩ ባለ ቃልኪዳኖች እንደማለት ናቸው። ረሱሉ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንኑ እውነታ እንዲህ ሲሉ ያስቀምጣሉ፡-

"ድል ከትዕግስት ጋር መሆኑን እወቅ።" (ቱርሙዚ)

## 4. *ከወንጀል ዓለም መፅዳት*

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡-

*"ማንኛውም ሙስሊም በእሾህ መወጋትም ይሁን ከዚያ በላይ የሆነ ችግር አይደርስበትም ልክ ዛፍ ቅጠሉን እንደሚያራግፍ አላህ (ሱ.ወ) ሀጥያቱን ያራገፈለት ቢሆን እንጂ።" (ቡኻሪና ሙስሊም)*

አላህ (ሱ.ወ) በባሪያው ላይ ፈተናን ካከታተለና ባሪያው ከታገሰ አላህ (ሱ.ወ) ለእርሱ በርካታ መልካም ነገርን ፈልጎለታል፤ ታላቅ ስኬትንም ሽቶለታል ማለት ነው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንኑ አስመልክተው እንዲህ ይላሉ፡-

"በወንድ ሙእሚንም ሆነ ሴት ሙእሚን ሕይወት፣ ልጅና ገንዘብ ላይ ፈተና ከመከሰት አይወገድም ምንም ወንጀል ሳይኖራቸው አላህን የሚገናኙ ቢሆን እንጂ።"[1]

ፉደይል ኢብን ዒያድ –ታላቁ የኢስላም ሊቅ– ይህንን ሐዲስ ከሰሙ በኋላ የሚከተለውን ግንዛቤ አሰፈሩ፡- "አንድ አባወራ የቤተሰቡን ደህንነት መልካም ነገሮችን በማሟላት እንደሚንከባከበው ሁሉ አላህ (ሱ.ወ) ደግሞ የባሮቹን አካል የሚንከባከበው በፈተና ነው።"

እናም ሙእሚን ፈተናን ኒዕማ (ፀጋ) አድርጎ ይመለከታል። ሙከራዎችን ስጦታ አድርጎ ይቆጥራል። ስቃይን መድኃኒት አድርጎ ያስባል። ምናልባት መድኃኒቱ መራር ሆኖ ዳሩ ግን መዳን የሚቻለው እሱን በመጎንጨት ብቻ ይሆናል። እንዲህ ሲሆን የሚከተለው ድምዳሜ ላይ ይደርሳል፡-

"ድህነት የዙህድ (የዚህን ዓለም ሕይወት መናቅ) አንድ በር ነው፤ በሽታ ከጂሃድ ዓይነቶች አንዱ ነው፤ ከአላህ ውጭ ከሆነ አካል ተስፋ መቁረጥ የትዕግስት ሌላው መንገድ ነው፤ ሀዘን የተስፋ ምልክት ነው።"

ከዚህም አልፎ መከራዎች በግለሰቡ ስብዕና ላይ ከመከራው በፊት የማያውቃቸውን አዳዲስ መልካም ባህሪያት ያላብሱታል። በተለየ ሁኔታ ሥነ-ምግባሩን ያንፁታል። አዲስ ማንነት ይገነባል። አሽ-ሸዕቢይ የተሰኙ ታላቅ ዓሊም በሚገርም ተምሳሌት ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፡-

"መከራና እንቁላል ተመሳስሏቸው አስደናቂ ነው። እንቁላል ውስጧ ላለው ጫጩት እንደ እስር ቤት ነች። ዳሩ ግን አምቃ ይዛ የተሟላ አካል እስኪገነባ ድረስ አስፈላጊውን ሁሉ ትሰጠዋለች። የተወሰነች ጊዜ መታገስ ብቻ ይጠበቅበታል። ግቡ ላይ የሚያደርሰው በመሆኑ

---

[1] ቲርሙዚይ

ሁኔታውን ወደ መቀበል ይኖርበታል። ጊዜው ሲደርስ እንቁላሉ ይሰበርና አዲስና የተሟላ ፍጡር ይወጣል።”

መከራ በሰው ልጅ ላይ ቢዘንብ ትዕግስት ካለ የመቋቋም አቅሙ ይጨምራል። ተራራ የማይችለውን ሊሸከም፣ ብረትን ባጣመመ ፈተና እንኳ ላይበገር፣ በቃጠሎ እንኳ ላይሟሟ የሚያስችለው አቅም ይኖረዋል። ዩሱፍ የደረሰባቸው በደል ተጋልጦ ንፅህናቸው የተረጋገጠው ከዓመታት እስር በኋላ መሆኑን አስታውስ።

በፈተና የተዘራው መልካም የሙእሚን ስብዕና ሊፋፋ የሚችለው የሶብር ውሃ ከጠጣ ብቻ ነው። በአንፃሩ በተፈታኙ ልቦና ውስጥ ተስፋ መቁረጥን ያስከተለች ፈተና፣ በምላሱ ላይ ማማረርን ያመጣች መከራ፣ ቀድሞ የነበረን የመልካም ሰብዕና ዘር ትነቅላለች እንጅ አትተክልም፤ ትጎዳለች እንጅ አትጠቅምም፤ ታጠፋለች እንጅ አታለማም።

## 5. የዲን መሪነት ይገባዋል

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፦

﴿وَجَعَلْنَا مِنْهُمْ أَئِمَّةً يَهْدُونَ بِأَمْرِنَا لَمَّا صَبَرُوا﴾ السجدة: ٢٤

*“ብታገሱና በተአምራታችን የሚያረጋግጡ በኾኑም ጊዜ፥ ከነርሱ በትዕዛዛችን የሚመሩ መሪዎች አደረግን፤” (አስ-ሰጅዳህ: 24)*

አላህ (ሱ.ወ) ትዕግስትን ለዲን መሪነት ቅድመ-ሁኔታ አድርጎታል። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመሪዎች ሁሉ መሪ ነበሩ። በርግጥም እርሳቸው የሚንቀሳቀስ የትዕግስት ተራራ ነበሩ። ትዕግስት ሰው ቢሆን ኖሮ ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ) ይቀናባቸው ነበር። ሆዳቸው ላይ ሁለት ድንጋይ ለማሰር ያስገደደ ድህነትና ረሃብ ከታጋሽነት ፈፅሞ አላስወጣቸውም። ባለቤታቸውንና ልጃቸውን በሞት ሲነጠቁም ታግሰዋል። በህዝባቸው የደረሰባቸውን ድብደባና ስድብ ታግሰዋል። ከውድ ሀገራቸው ሲባረሩ ታግሰዋል። የሚወዷቸው ጓደኞቻቸው (ሶሐቦች) ፊታቸው ላይ ሲገደሉና አካላቸው ሲቆራረጥ በዓይናቸው አይተው ታግሰዋል። ከፍጡራን ሁሉ ይበልጥ በሚወዷት ባለቤታቸው ዓኢሻ (ረ.ዐ) እና በእርሳቸው ክብር ላይ

የተቃጣውን የሙናፊቆች የስም ማጥፋት ዘመቻ ታግሰዋል፡፡ በዚህ ሁሉ መከራ ላይ ታገሱና ይህን የመሠለ ታላቅ ውርስ ትተው አለፉ፡፡ የረሱላችን (ሰ.ዐ.ወ) ውርስ የሚከፋፈለው ወደ እርሳቸው ባለን ቅርበት ልክ ነው፡፡ በትዕግስት መጠንህ ልክ ለእርሳቸው ያለህ ቅርበት ይወሰናል፡፡

- ኢማሙ አህመድ ኢብን ሐንበል (አላህ ይዘንላቸውና) በሐቅ ላይ በመፅናትና በመከራ ላይ በመታገስ ከአላህ ተዓምራት አንዱ ናቸው፡፡ መከራውን የተሸከሙት "ቁርኣን የአላህ ቃል ነው" በሚለው አቋማቸው ሳቢያ ነበር፡፡ በርግጥም ይህ አቋማቸውና በደረሰባቸው መከራ አለመንበርከካቸው ኢስላምን በባዕድ አስተሳሰብ ከመበረዝ ለመታደግ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ዑለማዎች እንዲህ ሲሉ ይህንኑ እውነታ ይገልፁታል፡- "አላህ ዲኑን እጅግ አደገኛ በሆኑ ጊዜያት በአቡበክር አስሲዲቅና በኢማሙ አህመድ አማካኝነት ረድቶታል፡፡ ይህም አቡበክር ዘካን በከለከሉ ሰዎች ላይ የወሰዱት አቋምና ኢማሙ አህመድ ደግሞ በቁርኣን የአላህ ቃል መሆን ላይ የነበራቸው አቋም ነው፡፡" ኢማሙ አህመድ በዚህ ትዕግስታቸው ምክንያት ለሁሉም ህዝብ መሪ (ኢማም) ለመሆን በቁ፡፡ የወቅቱ አምባገነን መሪዎች ጡንቻ ኢማሙ በሕይወት እያሉ መሪነታቸው ግልፅ እንዳይወጣ ቢያደርግም መሪነታቸው በህልፈታቸው ጊዜ ይፋ ሆኗል፡፡ እናም ወደ መቃብር የሸኛቸው ህዝብ ቁጥር አራት ሚሊዮን እንደነበር ይነገራል፡፡ ያኔ የጊዜ ቆጣሪ ሰዓታት የቆሙ ይመስላሉ፡፡ በግዳድ የሕይወት ዑደቷ ፀጥ አለ፡፡ በርሳቸው ጀናዛ ላይ የሚሰገደው ሶላት ከንጋት ጀምሮ የተጠናቀቀው ፀሐይ ስትጠልቅ ነበር፡፡ ለቅሶና የሀዘን ቁጭቱ ከአራቱም የሕብረተሰብ ክፍል ይሰማል፤ ከሙስሊሞች፣ አይሁዶች፣ ክርስቲያኖችና መጁሶች፡፡[1] በኢማሙ ሞት ያላዘነ አልነበረም፡፡ ኢማሙ አህመድ ለሁሉም እምነት ተከታይ ምርጥ አባት ነበሩ፡፡[2] በአላህ እምላለሁ

---

[1] መጁሶች፡- እሳት አምላኪያን

[2] ኢማሙ አህመድ ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር የነበራቸው በጎ ግንኙነት ያስተውሏል፡፡ (ተርጓሚው)

ይህ ከአኼራ በፊት ያለ ታላቅ ዱንያዊ ክብር ነው፡፡ የኢማሙ አህመድ ጀናዛ በሙሾ አውራጆች ወደ መቃብር የሚሸኝ አስክሬን አልነበረም፤ በአፍቃሪዎች ታጅቦ በጉጉት ወደ ምትጠብቀው ጀነት ለመድረስ የተሞሸረ ሙሽራ እንጅ፡፡

የትእግስትን መጨረሻ በዓይነ-ሕሊናህ ሳለው፡፡ መጀመሪያው ይቀልሃል፡፡ ያኔ ኢማም አህመድና ወንድሞቻቸው የደረሱበት ደረጃ ላይ ትደርሳለህ፡፡

## 6. ምፅዋት የሚሰጠው ለድሆች ነው

አንዳንድ ሰዎች አላህን የሚገዙት በተለዩ ጊዜያት ብቻ ይሆናል፡፡ መስጂዶችን የሚያውቋቸው በጁሙዓ ብቻ ይሆናል፡፡ ታዲያ እንዲህ ዓይነት ከአላህ የሸሹ ግለሰቦች ወደ አላህ ይመለሱ ዘንድ መከራ ሊያወርድባቸው ይችላል፡፡ እናም መከራው ወደ ንጉሱ ቤተ-መንግስት የሚያደርሰውን ካርታ ይሰጣቸዋል፡፡ በዚህ አጋጣሚም የልመና እጃቸውን ከዘረጉ፣ የአላህን ውሳኔ ከወደዱና የትዕግስትን ልብስ ከለበሱ ጌታቸው ዘንድ የመግባት ፈቃድን ያገኛሉ፡፡ ጌታቸው ዘንድ ወንጀላቸውን ተናዘው ይቆማሉ፤ ድህነታቸውን ይገልጻሉ፤ ችሎታ አልባነታቸውን ያሳያሉ፤ ልመናቸውን ይደጋግማሉ፤ እንባቸው ጉንጫቸው ላይ ይፈሳል፤ ባሳለፉት ጊዜ ልባቸው በቁጭት ያራል፤ በጌታቸው ፍርሃት ውስጣቸው ይዋባል፡፡ ያኔ በእርግጥም በእነርሱ ላይ ምፅዋት (ሶደቃ) ይበቃላቸዋል፡፡

﴿إِنَّمَا ٱلصَّدَقَٰتُ لِلْفُقَرَآءِ﴾ التوبة: ٦٠

"ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች ነው፡፡" (አት-ተውባህ፡ 60)

## 7. የመወደድና የመመረጥ ምልክት

አላህ (ሱ.ወ) ክልክል ያደረጋቸው ነገሮች ሲደፈሩ አልያም ሕግጋቶቹ ሲጣሱ ይቀናል፡፡ እነኝህን ተግባራት የፈፀመ ግለሰብ ደግሞ መቀጣቱ አይቀሬ ነው፡፡ ቅጣቱ በዱንያ ላይ እያለ ሆኖ ከሠራው ወንጀል እንዲርቅና ተፀፅቶም ድጋሚ እንዳይፈጽም ሊያደርገው ይችላል፡፡ በሌላ

መልኩ ደግሞ ቅጣቱ በአኼራ ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ አንድም ዘለዓለማዊ ሲሆን፥ ዘለዓለማዊ ባይሆን እንኳ የመቅለል እድል የሌለው ከባድ ይሆናል። ምክንያቱም ከጥፋት የመመለሻ ጊዜው አልፏልና። እናም አላህ ከተወህና ወደ አኼራ ካሸጋገረብህ በእርግጥም ተቆጥቶብሃል፤ ጠልቶሃልም። እዚሁ ዱንያ ውስጥ በጥፋትህ ከቀጣህ በእርግጥም ወዶሃል፤ አቅርቦሃልም።

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡-

"አላህ በባሪያው ላይ መልካምን ከፈለገለት ቅጣቱን በዱንያ ያፈጥንለታል፤ አላህ በባሪያው ላይ መጥፎን ከፈለገለት ወንጀሉን ዝም ይለውና የቂያማ ቀን በወንጀሉ አሟልቶ ይቀጣዋል።"[1]

የዱንያን እጅግ ትልቁን ፀጋ አንዲት ጊዜ ጀሀነም ውስጥ መነከር የሚያጠፋው ከሆነ ይህ በእርግጥ ፀጋ ይሰኛልን?

በዱንያ ውስጥ ያለፈን እጅግ አስከፊ መከራ አንዲት ጊዜ ጀነት ውስጥ መነከር የሚያስረሳው ከሆነ ይህ በእርግጥ መከራ ነውን?

## 8. <u>ጀነት</u>

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሐዲሰል ቁድሲይ እንዲህ ይላሉ፡-

*"አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- በዱንያ ውስጥ የባሪያዬን ሁለቱን ውዶቹን (ዓይኖቹን) ስወስድበት እኔ ዘንድ ጀነት እንጅ ሌላ ምንዳ አይኖረውም።"[2]*

ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) በሐዲሰል ቁድሲይ "አላህ እንዲህ አለ" ብለዋል፡-

*"ከዱንያ ውስጥ የአንድ አማኝ ባሪያዬን ወዳጅ ወደ አኼራ ስወስድበት ትዕግስት በማድረግ ባሪያዬ ከእኔ ምንዳን ከጠበቀ ጀነትን እንጅ ሌላ ምንዳ የለውም።"[3]*

---

[1] ቱርሙዚይና ሓኪም
[2] ቲርሚዚ
[3] ቡኻሪ

ምናልባትም የመልካም ሥራ ሚዛንህ ቀልሎ የመጥፎ ሥራ ሚዛንህ ሲደፋ፥ ብናኝ ያክል ትዕግስት የታገስካት በመጨመሯ በዚህችው ትዕግስትህ የጀነት ሰው ልትሆን ትችላለህ፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚሉህን በፅሞና አድምጥ፡-

*"አንድ ባሪያ አላህ ዘንድ ከፍ ላለች ደረጃ ታጭቶ በመልካም ሥራው ደረጃዋን መድረስ ሲሳነው… አላህ በአካሉ ወይም በገንዘቡ ወይም በልጁ ላይ መከራን ያመጣበታል፡፡" መከራዋ ላይ በሚኖረው ትዕግስት ደረጃዋን ይደርሳል፡፡*[1]

አንድ ሙእሚን ፀጋ ማግኘትንም ሆነ ማጣትን አላህ በሚፈልገው መልኩ ካስተናገዳቸው፥ ሁለቱም ጀነት መግቢያ መንገዶች ናቸው፡፡ ይህ ማለት እንዲህ ነው፡- "ፀጋ ወደ አንተ ትመጣለች፡፡ የአላህ ውሳኔ የጣፋጭ ፍሬ ቅርንጫፏን ወደ እጅህ ያቀርብልሃል፡፡ አንተ ግን የስሩን ምንነት አታውቅም፤ የማወቅ አቅምም የለህም፡፡ ከዚያም ኒዕማዋ ትገለበጥና እጅህ መራር የሆነው ፍሬ ላይ ያርፋል፡፡ ይህም ሲሆን አንተ አታውቅም፤ አቅምም የለህም፡፡ አዋጅ! ኢማን ማለት እርግጠኝነት (የቂይን) መሆኑን እወቅ፡፡ ሁለቱም ቅርንጫፎች አላህ ዘንድ ያደርሱሃል የጣፋጩ ቅርንጫፍ አምልኮዎች የምላስና የተግባር ምስጋናዎች ናቸው፡፡ ይህ በስሜት ህዋስህ ስትቀምሰው እጅግ ጣፋጭ ነው፡፡ የመራሩ ቅርንጫፍ አምልኮዎች ደግሞ ትዕግስት (ሶብር) እና ወዶ መቀበል (ሪዷ) ናቸው፡፡ ይህንንም በሩሕህ ስትቀምሰው እጅግ ጣፋጭ ነው፡፡" (ሙስጦፋ ሷዲቅ አር-ሪፋዒ)

ጀነት ውስጥ ሁሉም ችግሮችና መከራዎች ይረሱና ደስታና ፍስሃ ብቻ ይቀራል፡፡

አቡ ሙዓዊያ አል-አስወድ ዕረፍታቸውን ሠውተው ለሌሊት ሶላት ሲነሱ ይህንን መሰል አስተሳሰብ ያንፀባርቁ ነበር፡፡ የጀነት ሰዎችን ያስቡና፡-

---

[1] አህመድና አቡዳውድ

"በዱንያ እያሉ የደረሰባቸው ችግር ሁሉ አልጎዳቸውም። ጌታቸው በጀነት ውስጥ ችግራቸውን ሁሉ ጠግኖላቸዋልና" ይሉ ነበር።